ይህ “ቃል” በሚል ርዕስ መስከረም 13 ቀን 2004 ዓም በዋሽንግተን ዲሲ በአቶ ቴዎድሮስ አበበ ተገጥሞ የቀረበውና እኔም ትንሽ ስንኞችን በመጨረሻዎቹ መስመሮች ላይ ጨምሬ በደም መና በሚለው የግጥም መጽሃፌ ውስጥ ያካተትኩት ሲሆን በጊዜው ገጣሚውን ወጣት ቴዎድሮስን በአካል አገኝቼው ፈቃደኛነቱን አረጋግጦልኛል።ይህ ጊዜ ተሻጋሪ መልእክት የያዘ ግጥም ለወቅቱ የሚመጥን ሆኖ ስላገኘሁት ይዤው ብቅ ብያለሁ።

" በህይወት ታላቁ ነገር ያሰቡትን መናገር ነው "

ማርቲን ሉተር ኪንግ (1929-1968)

አገሬ አዲስ

ቃል

የዘመናችንን ትልቅ ግድፈት፣

የብሶታችንን መሠረት፣

እውነቱን እውነት ማለት፣

ስህተቱንም ስህተት።

ስላቃተን ነው ጸንቶ መቆም፣

ለሃቅ ለማተብ፣ለቃል ኪዳን፣

በምስቅልቅል ሕያው ዙሪያ፣

በመሽከርከር የተጎዳን።

ትክክለኛውን ትክክል

ስህቱንም እንዲሁ፣

መናገር ብንችል ኖሮ

ሳንዘገይ ከወዲሁ፣

ስንት ነፍስ ባዳንን ነበር

ስንቱን እልቂት ባሶገድን።

ለሕዝብ፣ለሃገር ተስፋ ሆነን፣

ደግነትን ባሳደግን።

ፍርሃትን ተከናንበን፣

እውነትን ባናዳፍን

በጥቅም ተደልለን

ውሸትን ባናሰፍን።

ፍትህ ሲጓደል ሙብት ሲጣስ

ዐይኖቻችንን ባንጨፍን

ለዐቅመ ደካሞች ሰቆቃ

ጆሮአችንን ባንሸፍን።

ምናልባት ያጥር ነበር

የመከራ ዘመን ዕድሜው፣

የስደት፣የእንግልት ጉዞው፣

የረሃብ መለዮ ስያሜው።

"አዎ"ከሆነ "አዎ"

ካልሆነም ደግሞ "አይደለም"

ቃላችን ምልክት ቢሆን

የእውነት አርማ ማህተም

ምንኛ በተጠቀምን፣

ትውልዱንም በጠቀምነው

የሕይወትን ቀና መንገድ

አቅጣጫውን ባሳየነው።

የመልካም ሥራ መልካምነት፣

የእውነተኞችን ጀግንነት፣

የክፉን ተግባር ክፉነት

የግፈኞችን ማንነት፣

መናገር እየቸገረን

አይቶ እንዳላዩ ባናልፈው፣
ከሃላፊነት ሸሽተን፣
ሕሊናችንን ባናጎድፈው።
ቅጥፈት ባያሳንሰን
በቃላችን ብንረጋ
እምነትን ብንታጠቅ
ለቅዱስ ተግባር ብንተጋ
እንዴት በተለወጠች
ምድሪቱ ባማረባት
በመተሳሰብ አጊጣ
ፍትህ በሰፈነባት!
"አዎ"ከሆነ "አዎ"
ካልሆነም ደግሞ "አይደለም"
የኑሮ መሠረት ቢሆን
መመሪያዋ ለዚህች ዓለም።
ሰላም በነገሠ ነበር
ቅንነትም በተስፋፋ
ክፋትም በተወገደ
ጥርጣሬም በጠፋ።
ትክክል ፈራጅ ዳኛ
እውነት የሚናገር መሪ
ለሰብአዊነት የቆመ
ለተበደሉ ተጠሪ
ትሁት የሕዝብ አገልጋይ
ቀጥተኛ መስካሪ
ልቦናውን ያስገዛ

የሚንበረከክ ለፈጣሪ

እናገኝ ነበር ምናልባት

የማይቻል ነገር የለም

"አዎ" ን "አዎ" ማለት ብንለምድ

"አይደለም" ንም "አይደለም"።

የጥፋት ጎዳናን ተከትለን

ወደ ገደሉ ስናመራ

እኛነታችንን ጥለን

በውርደታችን ስንኮራ

ቆም ብለን ብናስተውል

ብናስብበት ለደቂቃ

የማይሆነውን አካሄድ

"አይሆንም!" ለማለት ብንበቃ።

መድሃኒት ይሆነን ነበር

ለሁላችንም ታላቅ ድል

ስህተቱን ስህተት ብንል

ትክክሉንም ትክክል።

አዎ!

የዘመናችን ትልቅ ግድፈት

የብሶታችን መሠረት

እውነቱን እውነት ማለት

ስህቱንም ስህተተ

አለመቻላችን ነው የጎዳን

የሚያውካት ይህችን ዓለም

"አዎ" ን "አዎ" አለማለት

"አይደለም" ንም "አይደለም"

የእኔ መደምደሚያ

ሌባውን ሌባ፣ አታላዩን አታላይ፣

ጨካኙን ጨካኝ ገዳዩን ገዳይ፣

አድር ባዩንም አድር ባይ፣

ጀግናውን ጀግና ፈሪውን ፈሪ፣

ብለን የምንናገር   ብንሆን እውነተኛ መስካሪ፣

በተለይም ስለሕዝብና ስለሃገር፣

በድፍረት እውነተኛውን ታሪክ እንናገር፣

ይሉኝታና ፍርሃት አድር ባይነት ይቅር።

መልካሙን ይዘን መጥፎውን ጥለን

በአንድነት አብረን ተባብረን፣

እራስ ወዳድነትንና ጎሰኝነትን ትተን፣፣

ወገንተኝነትንና ቡድናዊነትን ንቀን

እኔም አንተ፣አንተም እኔ ተባብለን፣

ካለፈውና ከአሁኑ ውድቀታችን ተምረን፣

እጅ ለእጅ ተያይዘን ፣

ለመጓዝ የተዘጋጀን እንሁን።

ያን ጊዜ ከስደትና ከውርደት እንድናለን፣

የተወደድን፣የተፈራንና የተከበርንም እንሆናለን፣